# አልቢኖ (ሻሾ) ልጆች የሚገኙበት ትምህርት ቤቶች እና መንደሮች አስተዳደር እና መምህራን የተዘጋጀ

ከ: ኤቭሪ ቻይልድ ሚኒስትሪስ (ሁሉም ህፃናት አገልግሎት) የተዘጋጀ
“ለተረሱ የአፍሪካ ህጻናት” ተስፋ የሚሰጥ ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅት
ህፃናት የማንኛውም ሀገር ዋንኛ እሴት፥ ከእግዝአብሔር የተሰጡ ሀብት ናቸውና

ለትምህርት ቤት አስተዳደሮች እና መምህራን:

ሰላም! ኢትዮጲያን ለማገልገል በተለይም ታዳጊዎችን ለማነጽ የምትሰሩት ስራ እጅጉን ይበረታል። ፈታኝ የሆነ የስራ መደብን መርጣችኋል። እግዝአብሔር በጥንካሬ እና በማስተዋል ይባርካቹ።

አሁን እየጻፍንላችሁ ያለው በትምህርት ቤታቹ ውስጥ የአልቢኒዝም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች ስላሉ ነው። አልቢኒዝም (ሻሾነት) በዘር የሚመጣ ተፈጥሮ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ይህ ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች የማየት አቅማቸው የተዳከመ ሲሆን በተጨማሪም እራሳቸውን ከፀሃይ ጨረር ካልተከላከሉ ለቆዳ ካንሰር ሊጋለጡ ይችላሉ።

የአልቢኒዝም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች ማንኛውም ሰው ያለውን የአስተሳሰብ ችሎታ ሲኖራቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ እስካረጉ ድረስ ሌሎች የሚኖሩትን እድሜ ርዝመት መኖር እና ለማህበረሰቡ ጥሩ ነገርን ማበርከት ይችላሉ።

እርሶ እግዚአብሄር የሰጦትን የኃላፊነት ቦታ በመጠቀም የእነዚህን ልጆች ህይዎት የተሻለ ማድረግ ይችላሉ። ይህም የሚቻለው የሚከተሉትን በማድረግ ነው :

- የአልቢኒዝም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች የክፍል ሰሌዳውን በሚገባ መመልከት የሚችሉበት አካባቢ መቀመጣቸውን ማረጋገጥ። ወደፊት ቀረብ ብሎ መቀመጥ በይበልጥ ለማየት ያመቻቸው እንደሆነ ወደ ፊት ተጠግተው እንዲቀመጡ ይፍቀዱላቸው።

- ትላልቅ የእጅ ጽሁፍ ወይም ደሞ በእጅ የሚያዝ ማጉያ መነፅር አንድአንድ ልጆችን ሊረዳ ይችላል። ልጆች ከፍ እያሉ ሲመጡ ይህን መጠቀም ካፈሩ ቢያንስ በቤታቸው ውስጥ በሚያጥኑበት ጊዜ እንዲጠቀሟቸው ያበረታቷቸው። ፎቶ ኮፒ የሚያደርጉ ቤቶችም አብዛኛውን ግዜ አንድን ጽሁፍ አስተልቀው ማባዛት ይችላሉ። በጋና አገር የሚገኝ ማህበር

የአልቢኒዝም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች በኮምፒዩተር የተፃፈ ጽሁፍ መጠኑ ከ18 ያላነሰ ሲሆን ብቻ በትክክል እንደሚታያቸው ገልፆልናል (አብዛኛዎቹ መጻሃፍት የሚታተሙት 11 ወይም 12 የጽሁፍ መጠን ይዘው ነው) ።

- ለብዙ የአልቢኒዝም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ጽሁፍን በትላልቅ ከመጻፍ ይበልጥ በደንብ እንዲታይ አድርጎ መጻፍ በተሻለ ይጠቅማል። ለምሳሌ ደማቅ እስክሪቢቶ ተጠቅሞ ንፁህ ነጭ ወረቀት ላይ መጻፍ ይበልጥ ጠርቶ ይታያል። ጥቁር ሰሌዳ ላይ የተጻፈን ነገር አርንጓዴ ሰሌዳ ላይ ከተጻፈ ነገር ይልቅ ለአልቢኖ ልጆች ለማንበብ ይቀላል የክፍል ሰሌዳን በውሃ አዘውትሮ በማጠብ ሰሌዳው ላይ የሚጻፍ ጽሁፍ የተሻለ እንዲታይ ማድረግ ይቻላል። ለስለስ ያለ ጠመኔ በደማቁ ለመጻፍ ይረዳል። እንዲሁም ደማቅ ቀለም ያላቸው ጠመኔዎችን መጠቀምም ይረዳል።

- የአልቢኒዝም ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች የአካል ማጎልመሻ ክፍለ ጊዜ ላይ እንዳይሳተፉ ፈቃድ በመስጠት ወይንም ደሞ ክፍለ ጊዜው የእነርሱን ሁኔታ ያገናዘበ ሆኖ መሰናዳት አለብት። የአልቢኒዝም ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች የአካል ጥንካሬያቸው እንደማንኛውም ልጆች ቢሆንም የፀሀይ ጨረር ከፍተኛ በሚሆንበት ሠዓት (ከጠዋቱ አራት ሠዓት እስከ ቀትር አስር ሠዓት ድረስ) ቆዳቸው ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል። ይህም ጉዳት እስከ ቆዳ ካንሠር ድረስ ሊደርስ ይችላል። እነዚህ ልጆች የአካል እንቅስቃሴዎችን ጥላ ስር ወይም ቤት ውስጥ ማድረግ ይችላሉ። ግዴታ ውጭ መሆን ካለባቸው ደግሞ እጀ̄ታው ሙሉ የሆነ ልብስ እንዲሁም ሙሉ ሱሪ እና ከፀሀይ መከላከያ ኮፍያ እንዲያደርጉ ይፈቀዱላቸው። በእንደዚህ መልኩ እርሶ የሚያደርጉት ትብብር የአልቢኒዝም ተፈጥሮ ያላቸውን ልጆች ለቆዳ ካንሰር እንዳይጋለጡ እና እንደማንኛውም ልጆች መልካም ህይወት እንዲኖሩ ያግዛሉ።

- የአልቢኒዝም ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች ውጭ በሚሆኑበት ጊዜ ጥቁር መነጽር እንዲያደርጉ ይፍቀዱላቸው። ይህ ዐይናቸው ላይ በፀሀይ ጨረር አማክኝነት የሚደርስ ጉዳትን ለመከላከል ይረዳል።

- እባኮን ካለማዎቅ የተነሳ በሌሎች ልጆች ከሚደርስባቸው ሹፈት እና ፌዝ ለመጠበት ይሞክሩ። የአልቢኒዝም ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች አልታመሙም ወይም ደግሞ እርጉማን አይደሉም። ልክ እንደማንኛውም ልጆች እግዝአብሔር ያሰበላቸውን እንዲሆኑ በማህረሰቡ ተቀባይነትን ማግኘት ይሻሉ። ምንም እንኳ የተዳከመ የማየት ችሎታቸው እንዲሁም በቀላሉ በፀሀይ ጨረር የሚጎዳ ቆዳቸው እንደ አካልጉዳት ሊቆጠር ቢችልም ጥቂት ለውጥ በማድረግ ብቻ እንደማንኛውም ልጆች ለማህበረሰብ ጥሩ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ። ትምህርት ቤት ውስጥ ስድብ ጭራሱን ሊከለከል ይገባል። በልጆች ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ ተፅእኖ እጅግ የላቀ ነው።

- ከፀሀይ ጨረር ለመከላከል ወይንም ደግሞ ከማየት ችሎታቸው ጋር በተያያዘ ከሚደረጉላቸው ልዩ እንክብካቤዎች ውጭ የአልቢኒዝም ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች ልክ እንደማንኛውም ልጆች የትምህርት ቤት ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል። እባኮን ሌሎች ልጆች የአልቢኒዝም ተፈጥሮ ያላቸውን ልጆች በጨዋታ ጊዜም ሆነ በትምህርት ላይ እንዲያሳትፏቸው ያበረታቷቸው። ይህ ለአልቢኖ ልጆች እድገት አስፈላጊ ነው።

- በትምህርት ቤት ሠልፍ ላይ ስለ አልቢኒዝም መነጋገር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በሁሉም ህፃናት አገልግሎት (ኤቭሪ ቻይልድ ሚኒስትሪስ) ተዘጋጅተው የቀረቡ የጥያቄ እና መልስ እንዲሁም ሌሎች አጋዥ ጽሁፎችን መጠቀም ይችላሉ። አንድ አንድ ነገሮች ተደጋግመው ሊነገሩ ይገባል። ለምሳሌ "አልቢኒዝም በሽታ ወይም ህመም አይደለም" "አልቢኖ ልጆች አደገግኛ አይደሉም" "አልቢኖ ልጆች ልክ እንደማንኛውም ልጆች በረከት እንጂ እርግማን አይደሉም" ወዘተ

በአልቢኒዝም ዙሪያ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሎት የዚህ ስራ አመራር ባልደሮቦቻችን ከእርሶ ጋር ለመነጋገር ደስተኞች ናቸው። በእነዚህ ልጆች ህይወት ላይ ለሚያደርጉት አስተዋፅኦ እና በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ላደረጉት ትብብር እጅግ አርገን እናመሰግናን።

**በሁሉም ህፃናት አገልግሎት (ኤቭሪ ቻይልድ ሚኒስትሪስ) ተዘጋጅተው የቀረቡ:**

ለአልቢኖ (ሻሾ) ልጆች ወላጆች ማስተማሪያ

ለአልቢኖ (ሻሾ) ልጆች ማስተማሪያ

ጥያቄና መልሶች በአልቢኒዝም (ሻሾነት) ዙሪያ

መምህራን ለአልቢኖ (ሻሾ) ልጆች ሊያረጉት የሚችሏቸው ነገሮች (ይህ ሰነድ ማለት ነው)

ከወላጅ ወይም አሳዳጊ ጋር ወደ ቢሮዎቻችን ለሚመጡ እና ለሚመዘገቡ ልጆች የሚሰጡ የፀሃይ መነጽር እንዲሁም ሌሎች እርዳታዎች

ecmafrica@ecmafrica.org

www.ecmafrica.org

ከጊዜ ወደ ጊዜ ለሚወጡ አዳዲስ መረጃዎች ድህረ ገጻችንን ይመልከቱ።